184

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Foreign Affairs

ቀን 10 ነሐሴ 2012
Date
ቁጥር DMI/6/4/12
No.

ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን
ለፌዴራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ባለስልጣን
ለኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት
አዲስ አበባ

ሮም ከሚገኘው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ በተጻፈ ደብዳቤ Attens Coffee Festival በሚል ከSeptember 26-28/2020 በግሪክ አቴንስ ከተማ በሚካሄደው ኤግዚቢሽን በርካታ ጎብኚዎች የሚሳተፉበት፣ የቡና ባለሙያዎች ሴሚናር የሚሰጥበት፣ የተለያዩ የቡና ማሽን ኤግዚብሽን የሚካሄዱበት እና ሌሎችም ከቡና ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በኤክዚቢሽኑ እንደሚካሄድ ገልጾ፤ በሀገራችን ያሉ የቡና አምራቾች እና ላኪ ድርጅቶች ቦታ በመከራየት መሳተፍ እንዲችሉ መረጃው ለሚመለከተው እንዲደርስ ጠይቀዋል፡፡

በመሆኑም በእናንተ በኩል ተገቢው እንዲደረግ እየጠየቅን፣ ለአፈጻጸም ያመች ዘንድ ከሚሲዮኑ የደረሰንን ደብዳቤ ኮፒና ሌሎች ተያያዥ ሰነዶች 11 ገጽ በዚህ ደብዳቤ ሽፕነት አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሙንተሃ ጀማል ሰዩድ
የውጭ ንግድና የቱሪዝም ማስፋፊያ
ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል

አባሪ፡- የተጠቀሰው 11 ገጽ

ግልባጭ፡-
የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ቋሚ ተጠሪ ጽ/ቤት
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣

683
የገቢ ደብዳቤ
የተጻፈበት ቀን 9/12/2012
የደብዳቤው ቁጥር DMI/6/4/12
የደረሰበት ቀን 12/12/2012

ፋክስ ቁጥር +251 115 51 43 00 Fax
393
+251 115 51 73 45
E-mail: Info@mfa.gov.et
አዲስ አበባ፡-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ኤምባሲ - ሮም

EMBASSY OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ROME

ቁጥር NO. 7/646/2012
ቀን DATE 17/10/2012

ለውጭ ንግድና የቱሪዝም ማስፋፍያ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የቡና ኤግዚቢሽን መሳተፍን ይመለከታል፤

በግሪክ አቴንስ ከተማ ከSEPTEMBER 26-28, 2020 "ATHENS COFFEE FESTIVAL" በሚል የቡና ኤግዚቢሽን ይካሄዳል። ይህ ኤግዚቢሽን ለአምስተኛ ጊዜ የሚካሄድና ከ150 በላይ የቡና አቅራቢ ድርጅቶች(Exhibitor) የሚሳተፉበት፣ በቀን እስከ 8000 ጎብኝዎች የሚኖሩት፣ የቡና ባለሙያዎች(Coffee Professional) ሴሚናር የሚሰጥበት፣ የተለያዩ የቡና ማሽን ኤግዚቢሽን የሚካሄዱበት እና ሌሎችም ከቡና ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በኤግዝቢሽኑ የሚቀርቡ እንደሆነ አዘጋጁ ከላከልን መረጃ ለማወቅ ችለናል።

ስለሆነም በአገራችን ካሉ የቡና አምራች እና ላኪ ድርጅቶች በዚህ ኤግዚቢሽን ላይ Stand በመከራየት ቢሳተፉ የአገራችንን ቡና ከማስተዋወቅ ባለፈ የንግድ ትስስር ለመፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ ለመሳተፍ ፍላጎቱ ያላቸው ከአዘጋጁ ያገኘነውን የኤግዚቢሽን ብሮሸር ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን እየገለጽን በእናንተ በኩል የሚመለከታቸው ድርጅቶች እና ማህበራት እንዲደርሳቸው ቢደረግ እና መሳተፍ የሚፈልጉ ካምፓኒዎች "Athens Coffee Festival 2020" coffeefestival@forumsa.gr ኢ-ሜል በመላክ እንዲሁም Website:- www.athenscoffeefestival.gr በመመልከት መነጋገር የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

አባሪ:- 10 ገፅ

ዘነቡ ታደሰ ወልደፃዲቅ
ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ
ሥልጣን አምባሳደር